# ለ2021 ሜሞሪያል ዴይ ኮንፍረንስ ቁልፍ መግለጫዎች

የእውነትን ፍጹምነት ለማጽናት
እና በአሁኑ ክፉ ዘመን ለእውነት ለመመስከር
እውነትን ማወቅ እና ለእውነት ፍጹም መሆን ያስፈልገናል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተዘገቡ እና በሚገኙ
መንፈሳዊ ሃቆች ላይ የእውነት መንፈስ፣ የእውነታ መንፈስ ሲያበራ
እውነትን፣ እውነታን እንቀበላለን፤
በየማለዳው በተጻፈው ቃል ውስጥ ያለውን ሕያው ቃል መንካት
እና መለኮታዊው እውነታ፣ በሂደት ያለፈው ሦስታንዱ አምላክ
እንደ ሚተገበረው ቃል ወደ ማንነታችን ውስጥ የተሰረጸብን መሆን እንችላለን።

ለመለኮታዊው ኢኮኖሚ መጠናቀቅ
በመለኮታዊው እውነት ልንቀናበር እና
ለመለኮታዊው እውነት መንገድ እና ለመለኮታዊው እውነት መሰራጨት
ፍጹም ልንሆን ያስፈልጋል።

የጌታ ምለሳ የእውነት ብርሃን ምለሳ ነው፣
ዛሬ በምድር ላይ እጅግ አስቸኳዩ ፍላጎት የዚህ ዘመን እውነት ነው፤
የቤተ ክርስቲያን መጨመር በእውነት መሰራጨት ላይ ይመረኮዛል፣
ስለዚህ ለቤተ ክርስቲያን መባዛት እና መሰራጨት ሁላችንም እውነትን ለመማር
እና ለሌሎች ክርስቶስን ለማገልገል ጊዜ ማጥፋት አለብን።

*© 2021 Living Stream Ministry*

**አጠቃላይ ርዕስ፡-**
**እውነትን ማወቅ፣**
**ለእውነት ፍጹም መሆን**
**እና በአሁኑ ክፉ ዘመን እውነትን ማወጅ**

መልእክት አንድ

**እውነትን ማወቅ፣**
**ለእውነት እና የእውነትን ፍጹምነት**
**ለማጽናት ፍጹም መሆን**
**እና በዓለም የአሁኑ ዘመን ለእውነት መመስከር**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- ዮሐ. 18፡37፣ ኤፌ. 2፡2፤ ሮሜ 12፡2፤ 1 ዮሐ. 5፡19-20

**I. የጌታ ምለሳ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ በተገለጠው መሠረት የመለኮታዊ እውነቶች ምለሳ ነው—2 ጢሞ. 3፡16፡-**

ሀ. እውነት ማለት ሦስታንዱ አምላክ ከቃሉ ጋር ነው—ዮሐ. 1፡1፣ 14-17፤ 14፡6፣ 16-17፤ 15፡26፤ 16፡13፤ 17፡17፤ 18፡37።

ለ. በቃሉ ውስጥ ያሉ ብዙ እውነቶች ጠፍተዋል፣ ሰዎች በተሳሳተ መንገድ ተረድተዋቸዋል፣ በተሳሳተ መንገድም ተተግብረዋል፤ በመሆኑም የጌታ ምለሳ አስፈላጊነት አለ—2 ጢሞ. 2፡15።

ሐ. ምለሳው ከፍተኛው እውነት—ባለፉት ክፍለ ዘመናት የተመለሱ እውነቶች መጠናቀቅ የሆነ እውነት—አለው—ቁ. 2፣ 15።

**II. በዮሐንስ ጽሑፎች ውስጥ *እውነት* (*አሌቲያ*) የሚለው የግሪክ ቃል እንደ መለኮታዊው መገለጥ ይዘት፣ በቅዱስ ቃሉ የተላለፉትንና የተገለጡትን የመለኮታዊ ኢኮኖሚ እውነታዎችን በሙሉ ያመለክታል—ዮሐ. 17፡17፤ 18፡37፡-**

ሀ. እውነት ብርሃን እና ፍቅር የሆነው፣ ርስታችን ይሆን ዘንድ የመለኮታዊ ነገሮች እውነታ ለመሆን *ሥጋ* የለበሰው እግዚአብሔር ነው—1፡1፣ 4፣ 14-17።

ለ. እውነት *ሥጋ* የለበሰው እግዚአብሔር የሆነው እና የመለኮት ሙላት ሁሉ በእርሱ በሰውነት የሚያድርበት፣ የእግዚአብሔር እና የሰው፣ በብሉይ ኪዳን ያሉ ምሳሌዎች፣ ስዕሎች እና ጥላዎች ሁሉ እና የመለኮታዊና የመንፈሳዊ ነገሮች ሁሉ እውነታ የሆነው ክርስቶስ ነው— ቆላ. 2፡9፣ 16-17፤ ዮሐ. 4፡23-24።

ሐ. እውነት እንደ የክርስቶስ እና እንደ የመለኮታዊው መገለጥ እውነታ የተለወጠው ክርስቶስ የሆነው መንፈስ ነው—14፡16-17፤ 15፡26፤ 16፡13-15።

መ. እውነት የእግዚአሔርን እና የክርስቶስን እንዲሁም የመለኮታዊና የመንፈሳዊ ነገሮችን ሁሉ እውነታ የሚገልጥልን እና የሚያስተላልፍን መለኮታዊው መገለጥ የሆነው የእግዚአብሔር ቃል ነው—17፡17።

ሠ. እውነት እንደ ሙሉው ወንጌል እውነታ የምናምንበት ነገር ተጨባጭ ንጥረ-ነገሮች የሆኑት የእምነት (የማመን) ይዘቶች ነው—ኤፌ. 1፡13።

ረ. እውነት በፍጥረት እና በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተገለጠው እግዚአብሔርን፣ አጽናፍ-ዓለምን፣ ሰውን፣ ሰው ከእግዚአብሔር እና በአጠቃላይ ከሰዎች ጋር ያለውን ግንኙነት፣ ሰው ለእግዚአብሔር ያለበትን ግዴታ የሚመለከት እውነታ ነው—ሮሜ 1፡18-20፤ 2፡2፣ 8፣ 20።

ሸ. እውነት፣ የእግዚአብሔር መለኮታዊ ሰናይ ባህሪያት፣ የሰው የስብዕና ሰናይ ባህሪያት እና የመለኮታዊው እውነታ ውጤት የሆኑት እውነተኝነት፣ ሐቀኘትነት፣ ቅንነት፣ አለማስመሰል፣ መታመን የሚችል እና ታማኝነት ነው—3፡7፤ 15፡8፤ 2 ቆሮ. 11፡10፤ 1 ዮሐ. 3፡18።

ቀ. እውነት የሚያመለክተው እውነት ወይም እውን የሆኑ ነገሮችን፣ የጉዳዮችን (የሃቆችን) እውነተኛ ወይም እውን የሆነ ሁኔታን፣ የውሸት፣ የማታለል፣ የማስመሰል፣ የግብዝነት፣ እና የስህተት ተቃራኒ የሆነውን እውነታን፣ ትክክለኛነትን ነው—ማር. 12፡32፤ ዮሐ. 16፡7፤ ሮሜ. 1፡25።

**III. መለኮታዊው እውነት ፍጹም ነው፣ እኛም ለእውነት እና የመለኮታዊውን እውነት ፍጹምነት ለማጽናት ፍጹም መሆን አለብን—3 ዮሐ. 3-4፣ 8፡-**

ሀ. ለእውነት ፍጹም መሆን ማለት፣ ስሜቶችን ወደ ጎን ማድረግ፣ የግል ግንኙነቶችን ቸል ማለት እና ለእኔት አለመቆም ማለት ነው—ማቴ. 16፡24-25፤ 1 ጴጥ. 1፡22፡-

1. እውነት ብቸኛው መስፈርት ነው፣ ራሳችንን ለመቃወም ከእውነት ጎን መቆም አለብን፤ የእውነትን ፍጹምነት ማጽናት የሚቻለው ከራሳችን ነጻ ስንወጣ ብቻ ነው—ዮሐ. 8፡32፤ 2 ዮሐ. 2፤ 3 ዮሐ. 3-4።
2. እውነት ለእኛ ፍጹም የሆነ ነገር ካልሆነ፣ እግዚአብሔርን አናውቀውም፣ የእግዚአብሔርንም ቃል አናውቀውም—2 ተሰ. 2፡10፤ 1 ዮሐ. 5፡20።
3. ለእውነት ፍጹም ካልሆንን፣ የእግዚአብሔርን እውነት ለራሳችን ወይም ለራሳችን መሻቶች እንሰዋዋለን—ምሳ. 23፡23።
4. የእግዚአብሔርን እውነት ማክበር እና የእውነት መንገድ መውሰድ እና እውነትን በምንም መንገድ አለማመቻመች አለብን—2 ጴጥ. 2፡2።

ለ. ለውጫዊዎቹ እውነቶች እና ለውስጠ-ልምምዳዊዎቹ እውነቶች ፍጹም መሆን አለብን—ዮሐ. 8፡32፤ 14፡6፡-

1. በመጽሐፍ ቅዱስ ያሉት እውነቶች ውጫዊ ገጽታና ውስጠ-ልምምዳዊ ገጽታ አላቸው፤ ውጫዊው ገጽታ ለውስጠ-ልምምዳዊው ገጽታ ነው—ሮሜ 8፡34፣ 10፤ ቆላ. 3፡1፤ 1፡27።
2. ውጫዊዎቹ አስተምህሮዎች ለውስጠ-ልምምዳዊዎቹ እውነቶች ናቸው፣ ውስጠ-ልምምዳዊዎቹ እውነቶች ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን ለማፍራት ናቸው—2 ዮሐ. 1-2፣ 4፤ 3 ዮሐ. 3-4፣ 7-9።
3. ጌታ በቅዱሳት መጽሐፍት ውስጥ ያሉትን ውስጠ-ልምምዳዊዎቹ እውነቶች፣ በተለይ ደግሞ ሦስታንዱን አምላክና ቤተ ክርስቲያንን የሚመለከቱትን የእውነትን ውስጠ-ልምምዳዊው ገጽታ መመለስ ይፈልጋል—ዮሐ. 1፡14፣ 14፡16-20፤ 1 ጢሞ. 6፡15-16፤ 2 ጢሞ. 4፡22፤ 3፡15-16።
4. ብዙ ወሳኝ ውስጠ-ልምምዳዊው እውነቶች ተቀብረዋል፣ ነገር ግን በጌታ ምለሳ እነዚህ እውነቶች የተመለሱ፣ ከሞት-የተነሡ እውነቶች ይሆኑ ዘንድ ከሞት-ተነሥተዋል—ዮሐ. 17፡17፤ 18፡37።

**IV. "በዚህ የዓለም ዘመን" ለእውነት ስንመሰክር "የማያምኑትን አሳብ ያሳወረውን፣" "የዚህ ዓለም ገዢ፣" "የዚህ ዓለም አምላክ" የሆነውን ሰይጣንን፣ ዲያብሎስን፣ የውሸቶች አባትን በመዋጋት ከድል-ነሺው ክርስቶስ ጋር አንድ ነን—ኤፌ. 2፡2፤ ዮሐ. 8፡44፤ 12፡31፤ 2 ቆሮ. 4፡4፡-**

ሀ. የዲያብሎስ ባህሪ ውሸት ነው፣ ይህም ሞትና ጨለማን ያመጣል፤ ከጨለማ ጋር የእውነት ተቃራኒ የሆነው ውሸት አለ—ዮሐ. 8፡44፡-

1. ዲያብሎስ "እውነትም በእርሱ ስለ ሌለ በእውነት አልቆመም"—ቁ. 44።
2. ሰይጣናዊው ጨለማ ከመለኮታዊው ብርሃን በተፃራሪ ነው፤ ሰይጣናዊው ውሸት ደግሞ ከመለኮታዊው እውነት በተፃራሪ ነው።
3. መለኮታዊው እውነት የመለኮታዊው ብርሃን መገለጥ እንደሆነው ሁሉ ሰይጣናዊው ውሸትም የሰይጣናዊ ጨለማ መገለጥ ነው—ዮሐ. 8፡12፣ 44።

ለ. "የዚህ ዓለም አምላክ" አሳቹ፣ የዚህ ዘመን ገዢ ሰይጣን ነው፤ እርሱ የማያምንኑትን ሃሳብ፣ አእምሮ በማሳወር የዛሬውን ዓለም ይገዛል የሰውንም አምልኮ አጥብቆ ይፈልጋል—2 ቆሮ. 4፡4።

1. በ 2ኛ ቆሮንቶስ 4፡4 *አሳወረ* የሚለው የሰውን መረዳት መጋረድ ማለት ነው።
2. በዚህ ጥቅስ ውስጥ *አሳብ* የሚለው የሚያመለክተው የአእምሮ መረዳትን ነው።

ሐ "ዓለም በሞላው በክፉው ተይዟል"—1 ዮሐ. 5፡19።

1. መላው ሰይጣናዊው የዓለም ስርዓትና የዓለም ሕዝብ፣ የወደቀው የሰው ዘር፣ በሰይጣን፣ በክፉው በማይገባው እና በአታላይ እጅ ሥር ምላሽ ባለመስጠት ተቀብለውት ተቀምጠዋል።
2. በግሪኩ ክፉው የሚለው የሚያመለክተው ቀስ በቀስ በስውር የሚጎዳ፣ ጎጂ በሆነ ሁኔታ ክፉ የሆነ፣ ሌሎች ክፉ እንዲሆኑ ተጽእኖ የሚያደርግን ማንነት ነው፤ ይህ ክፉው ዓለም ሁሉ የተያዘበት ሰይጣን፣ ዲያብሎስ ነው።
3. ይህ ክፉ ስርዓት፣ የሰይጣን መንግሥት፣ ጌታ በሥጋው በመሰቀሉ ገዢው፣ ሰይጣን ሲጣል ተፈርዶበታል—ዮሐ. 12፡31፤ 14፡30፤ 16፡11።

መ. በኤፌሶን 2፡2 *በዚህ ዓለም* የሚለው ከብዙ ዘመናት የተቀናበረውን ሰይጣናዊውን ስርዓት ያመለክታል፡-

1. ዘመን፣ የዓለም፣ የሰይጣናዊው ስርዓት ክፍል ነው።
2. በኤፌሶን 2፡2 *በዚህ ዓለም* የሚለው ሰዎችን አለአግባብ ለመያዝ እና ለመቆጣጠር እንዲሁም ከእግዚአብሔርና ከዓላማው ለማስቀረት የሚጠቀምበትን የሰይጣንን ስርዓት የአሁኑን እና ዘመናዊውን መልክ ያመለክታል።

3. በገላትያ 1፡4 *ክፉ ከሆነ ከአሁኑ ዓለም* የሚለው ኃይማኖታዊውን ዓለም፣ የዓለምን ኃይማኖታዊ ገጽታ ያመለክታል።

ሠ. በአሁኑ ዘመን ለእውነትን ለመመስከር ከፈለግን፣ በሮሜ 12፡2 ያለውን የጳውሎስን ትዕዛዝ ማክበር አለብን፡- “በአእምሮአችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ” (አ.መ.ት)፡-

1. መምሰል ማለት ከውስጣችን የማይወጣን ወይም ዳግም እንደተወለዱ የእግዚአብሔር ልጆች የውስጡ ማንነታችንን የማይወክል ውጫዊ መገለጥን መያዝ ነው—ዮሐ. 1፡12-13።
2. ከዓለም ለእግዚአብሔር የተለየን እኛ ከዚህ ዘመን ጋር አንድ አይነት መልክ እስከሚኖረን ድረስ ከዓለም ጋር መመሳሰል የለብንም።
3. የተዋሐደው መንፈስ ወደ አእምሮአችን እንዲሰራጭ በመፍቀድ በአእምሮአችን መንፈስ መታደስ አለብን፣ ከዚህም የተነሣ የአእምሮ መንፈስ ይሆናል፣ አእምሮአችንን፣ ስሜታችንን እና ፈቃዳችንን ወደ ውስጡ ማንነታችን እየተሠራ ባለው በአዲሱ ንጥረ-ነገር እንዲታደሱ ያደርጋል—ኤፌ. 4፡23፤ 1 ቆሮ. 6፡17፤ ሮሜ 12፡2።

ረ. “እንግዲህ ወገባችሁን በእውነት ታጥቃችሁ...ቁሙ፤” በእውነት መታጠቅ ለመላው ማንነታችን መጠንከር ነው—ኤፌ. 6፡14።

ሰ. ለመለኮታዊው እውነት መመስከር የምንችለው እውነተኛ በሆነው በእርሱ ውስጥ በመሆን እውነትን ስለምናውቅ ነው—1 ዮሐ. 5፡20።

1. የእግዚአብሔር ልጅ፣ ጌታ ኢየሱስ መጥቷል፣ እውነተኛውን እና ትክክለኛውን አምላክ እንድናውቀውም መረዳትን ሰጥቶናል—1 ዮሐ. 5፡20፡-
2. አንደኛ ዮሐንስ 5፡20 ሁለት ጊዜ “እውነተኛ በሆነው በእርሱ፣” እውነተኛ የሆነው፣ እውነተኛ ብሎ ይናገራል፡-
   ሀ. *እውነተኛ* የሚለው ስያሜ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ለእኛ ውስጠ-ልምምዳዊ መሆኑን፣ ውጫዊ የሆነው አምላክ በሕይወታችን እና በልምምዳችን እውነተኛው መሆኑን ነው።
   ለ. እውነተኛ የሆነው መለኮታዊው እውነታ ነው፤ እውነተኛ የሆነውን ማወቅ ማለት ይህን እውነታ በመለማመድ፣ በመደሰት እና የራስ በማድረግ መለኮታዊውን እውነታ ማወቅ ነው።
   ሐ. ቁጥር 20 የሚያመለክተው እግዚአብሔር ራሱ  የሆነውን መለኮታዊው እውነታ፣ በልምምዳችን የእኛ እውነታ መሆኑን ነው፤ የሆነ ጊዜ ውጫዊ የነበረው አምላክ ዛሬ ውስጠ-ልምምዳዊ እውነታ ሆኖልናል—ቁ. 6።

ሸ. እውነተኛ የሆነው እና የእውነታ መንፈስን ስለምናውቅ (ቁ. 20፤ 4፡6) እና እውነት የሆነው ክርስቶስ በውስጣችን ስለሚኖር፣ ሦስታንዱ አምላክም እኛን አምላክ-ሰዎች—የመጀመሪያው አምላክ ሰው የሆነው የክርስቶስ ርቢዎች—ለማድረግ በእኛ ውስጥ እየሠራ ስለሆነ፣ ጌታ ራሱ “እኔ ለእውነት ልመሰክር ስለዚህ ተወልጃለሁ ስለዚህም ወደ ዓለም መጥቻለሁ፤ ከእውነት የሆነ ሁሉ ድምፄን ይሰማል”(ዮሐ. 18፡37) ብሎ ሲናገር እንዳደረገው፣ እኛም ለእውነት መመስከር እንችላለን።

*© 2021 Living Stream Ministry*